ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

# ክብርት ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት ሶስተኛውን የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስትራቴጂካዊ እቅድ (2014-2018) ለባለድርሻ አካላት ለማስተዋወቅና ተጨማሪ የማዳበሪያ ግብዓት ለመሰብሰብ በተዘጋጀ መድረክ ያደረጉት ንግግር

ቀን፡- ሰኔ 08/2013 ዓ.ም

የስብሰባ ቦታ፡- ራዲሰን ብሉ ሆቴል

**አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ**

ረዘም ላለ ጊዜ የሚያገለግል የስትራቴጂክ እቅድ ሁለት አላማዎች አሉት፤ አንደኛው አላማ ከእለታዊ የኦፕሬሽን ስራዎች ወጣ ብሎ የዛሬ 5 ዓመት የት መድረስ እንፈልጋለን የሚለውን ግብ ለመለየት ሲሆን፣ ሁለተኛው አላማ ደግሞ ወደተባለው ግብ እንዴት ይደረሳል የሚለውን ማወቅ ነው፡፡

የስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት የነበረው እና ያለውን መረጃ ከግምት ያስገባ፣ በሌላ በኩል ግን ለየት ያሉ እና ወደፊት ተመልካች ሃሳቦችን የሚያስጨብጥ መሆን ይገባዋል፡፡

ይህን ፍላጎታችንን ለማሳካት ስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅቱ በውስጥ ባለሞያዎች ብቻ ሳይገደብ በአሁኑ ጊዜ ከፍ/ቤት ውጭ ያሉ ባለሞያዎች ክህሎት እና አስተያየት የተጨመረበት እንዲሆን የሚያስችል አካሄድ ተከትለናል፡፡ በዚሁ መሰረት (Advance Associate Upfront) የተባለውን አማካሪ ድርጅት በዚህ ስራ እንዲያግዝ እድል ተሰጥቶታል፡፡ ጎን ለጎን ስትራቴጂክ እቅዱ ተጨባጭ እና ተግባራዊ እንዲሆን እንዲሁም ላለፈው አንድ አመት ተኩል እየተተገበሩ ያሉትን የሪፎርም ስራዎች ያካተተ እንዲሆን የፍ/ቤቱ አመራሮች እና ባለሞያዎች የተሳተፉበት ኮሚቴ በማዋቀር ከአማካሪ ቡድኑ ጋር ላለፉት.... ወራት ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡

ረቂቅ ስትራቴጂክ እቅዱ ለፍ/ቤት አመራሮች እና ሰራተኞች ቀርበ ውይይቶች ተደርገውበታል፡፡ የማሻሻያ ግብዓቶችም ተሰጥተዋል፡፡ ባለፈው አስር ዓመት ፍ/ቤቱ “ሚዛናዊ የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና BSC” የተባለውን የማናጅመንት ሞዴል በሁለት የስትራቴጂክ እቅዶችን **ከ 2003-2007** እንዲሁም **ከ 2008-2012** ሲተገብር ቆይቷል፡፡

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

**ከ 2012** ጀምሮ ግን በዝርዝር የተቀመጡትን ግቦች ሰብሰብ እንዲሉ እና ለውጤታማነት አመቺ እንዲሆኑ በማድረግ ከልሰናቸዋል። **ከ 2012** ዓ.ም ጀምሮ የተቀመጡት ሰስቱ የፌዴራል ፍ/ቤት ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የዳኝነት ነጻነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነትን ማሻሻል
2. የዳኝነት ቅልጥፍና፣ ጥራት እና ተደራሽነትን ማሳደግ
3. እንዲሁም ለዳኝነት አገልግሎት የሚያስፈልጉ አስተዳደራዊ ድጋፎችን ማጠናከር ናቸው።

**2012** እና **2013** ዓ.ም የታቀዱት ፕሮግራሞች እና በጀቶች እንዲሁም የሪፎርም ስራዎች የተመሰረቱት በእነዚህ ግቦች ላይ ነበር። **ከ 2014** ጀምሮ የሚተገበረው ዛሬ በምንነጋገርበት ስትራቴጂ ሃገር አቀፍ ለውጦችን፣ የፍ/ቤቱ የለውጥ ራዕይ እና የተመረጡ የለውጥ ምሰሶዎችን ያማከለ ይሆናል። ስትራቴጂውም ለክልል ፍ/ቤቶቻችን እንደሞዴል ያገለግላል የሚል እምነት ስላለን የክልል ፕሬዝዳንቶች ዛሬ በመሃከላችን ተገኝተዋል።

እንደምታውቁት ዋነኛ የፍ/ቤት ተልዕኮ የሕግ የበላይነት እንዲከበር መስራት ነው። ፍ/ቤቶች ክርክሮች መቋጫ የሚያገኙበት መድረክ መሆናቸውን የሚታወቅ ሆኖ የፍ/ቤቶችን አላማ ለማሳካት መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የፍትህ አካላት ሚና ወሳኝ ነው። ዛሬ በመካከላችን የተገኛችሁት የዓቃቤ ሕግ፣ የፖሊስ እንዲሁም የማረሚያ ቤቶች ሃላፊዎች /ተወካዮች የሕግ የበላይነትን ለማሳካት ተደጋጋፊ ሚና እንዳለን ታውቃላችሁ። በፈጠርነው የጋራ መድረክም በተለይ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ረገድ ተደጋጋሚ ምክክሮችን እናደርጋለን። ከዚህ ጎን ለጎን የጠበቆች ሚናም ቁልፍ ነው። ስለዚህም ከዛሬ ውይይት በርከት ያሉ ገንቢ ግብዓቶችን እንጠብቃለን።

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

ስለህግ የበላይነት ካነሳሁ ሃገራችን ካለችበት የሽግግር ጊዜ እንዲሁም ከመጪው አገር አቀፍ ምርጫ አኳያ በድጋሚ መንግስትም ሆነ ሕዝባችን የሕግ የበላይነት የሚያመጣውን የሰላም፣ የልማት ትሩፋት በመገንዘብ ከመፈክር  ባለፈ ሁላችንም የሕግ የበላይነት ጠበቃ እና ተጠሪ እንድንሆን በድጋሚ መልዕክት ለማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡

የሕግ የበላይነት ሕግን መሰረት በማድረግ ነጻነት፣ እኩልነት እና እኩል እድልን ማረጋገጥን መሰረት ያደርጋል፡፡ የሕግ የበላይነት ተጠያቂነት ማረጋገጥንም ያካትታል፡፡ የህግ የበላይነት የመንግስትን ቅቡልነት ከፍ ያደርጋል፡፡ የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገር ኢንቨስተሮችን ያበረታታል፡፡

የአምስት ዓመት የፍ/ቤቱ እቅዳችን ራዕይ የሕዝብ አመኔታ ማግኘት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የማያቋርጥ ጥረት የሚጠይቅ እና በተግባራችን ላይ ተመስርቶ የሚገኝ እንጂ በስለት የሚሆን አይደለም፡፡

በነጻነት እና በገለልተኝነት መርሆ ላይ ተመስርቶ በመገንባት ላይ ያለው የዳኝነት ዘርፉ የሪፎርሙ ቁልፍ ራዕይ ነው፡፡ መንግስት እና ሕዝብ ያመኑበት ጉዳይ በመሆኑ በነጻነት፣ በገለልተኝነት እንዲሁም በተጠያቂነት መርሆዎች ላይ ተመስርተን ተልዕኮአችንን ለመወጣት ጥረት እያደረግን ነው፡፡

ነጻ ፍ/ቤቶችን መገንባት የሪፎርሙ ራዕይ ሲሆን በሌላ በኩል ነጻ ገለልተኛ እና ተዓማኒ ፍ/ቤቶች ደግሞ የዲሞክራሲ ሂደቱን ለመቅረጽ በጎ ተጽዕኖ የሚፈጥሩበት ጊዜ የደረሰ ይመስላል፡፡ ይህ ከተሳካ ለአገራችን የምስራች ነው፡፡ ለምሳሌ መጪው ምርጫን

አስመልክቶ ፍ/ቤቶቻችን የሚሰጡት ውሳኔ በዲሞክራሲ ሂደት ላይ በጎ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

ሌላ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው በዚህ አመት በጸደቀው የአስተዳደር ስነ-ስርዓት ሕግ መሰረት በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ የሚነሱ ክርክሮች እና የሚሰጡ ውሳኔዎች ናቸው፡፡ የእንዲህ አይነት ክርክሮች አላማ አስፈጻሚ አካላት የሚሰጧቸውን አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እና የሚያወጧቸው ደንብ እና መመሪያዎች ሕገ-መንግስቱን እና ሌሎች ሕጎችን የተከተሉ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡

በአስፈጻሚ አካላት በዘፈቀደ/ያለምንም ገደብ የሚሰጡ ውሳኔዎች የሚወጡ ደንብ እና መመሪያዎች በሕግ ሚዛን መፈተሻቸው የዲሞክራሲያዊ እና ተጠያቂ የመንግስት አስተዳደር ለመፍጠር የመጀመሪያ እና ታሪካዊ እርምጃ ነው፡፡ በአጠቃላይ መንግስት በተለይ ህግ አውጪው እንዲህ ያለውን ታሪካዊ እና ደፋር እርምጃ ሲወስድ እውቅና መስጠቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ፍ/ቤትን ጨምሮ ሁሉም ተቋማት ለሕግ ተገዢ መሆናችንን በየደረጃው እያስመሰከርን መሄድ ይኖርብናል፡፡ ፍ/ቤቶች በዲሞክራዊያዊ መንገድ መንግስት ያደረገውን የፖሊሲ ምርጫ ሕገ-መንግስቱን እና ሌሎች ሕጎችን ካልጣሰ በስተቀር ማክበር ግዴታችን ነው፡፡

ዳኞች የወጣው ሕግ ወይንም መመሪያ ከያዙት አስተሳሰብ፣ የሞራል፣ የሃይማኖትም ሆነ ሌላ እምነት ጋር አልተጣጣመም በሚል የስልጣን ክፍፍል መርህን ከጣሱ በገለልተኝነት

እንዳልተሰጠ ውሳኔ ሁሉ የተቀበሉትን ቃለ-መሃላ እንዳፈረሱ ይቆጠርባቸዋል። በአሁኑ ጊዜ አዲስ ልምምድ ውስጥ እየገባን ስለሆነ ጥንቃቄ እና ብስለት ያስፈልገናል።

ፍ/ቤቶቻችን፡-

- ነጻ (ማለትም ተቋማዊ እና ዳኝነታዊ ነጻነታቸው የተከበረ)
- ገለልተኛ (በነጻነት ሽፋን አድልዎ የማይፈጽሙ) እንዲሁም

ጠንካራ እንዲሆኑ እንፈልጋለን።

ፍ/ቤቶችን ነጻ እና ገለልተኛ ሆነው ጠንካራ ካልሆኑ የመጨረሻ ግባችን ወደሆነው ቅልጥፍናም ሆነ ውጤታማነት ላይ ለመድረስ አንችልም።

ዛሬ ላይ ሆነን ያለፈውን ሁለት ዓመት ስንመለከት ፍ/ቤቶቻችን በቅልጥፍና፣ በውጤታማነት እንዲሁም “ሰው ተኮር” (people centered) ለመሆን እንዲሁም በነጻነት እና በገለልተኝነት ረገድ የማይናቅ እርምጃ ወስደናል። እንደምታውቁት እንዲህ ያለው ግብ ቀጣይ የስርዓት ግንባታ የሚጠይቅ፣ እያደገ የሚሄድ ነው። ስራችን ተጀመረ እንጂ አላለቀም።

በ 5 ዓመቱ የፍ/ቤት ስትራቴጂ ከሚካተቱት ውስጥ መርጠሽ አንድ ግብ እና አንድ እሴት ጥቀሽ ብባል ግቦቹም ሆኑ እሴቶቹ ተመጋጋቢ በመሆናቸው አስቸጋሪ ቢሆኑም ሁለቱንም መጥቀስ እችላለሁ።

## በግብ ደረጃ፡-

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

ከቅልጥፍና በተጨማሪ የውሳኔ ጥራት እንዲሰመርበት እፈልጋለሁ፡፡ የውሳኔ ጥራት የስነ-ስርዓት ሕጎችን በመከተል መስራት፣ ተከራካሪዎችን በእኩልነት ማስተናገድ፣ በእኩልነት ማስተናገድ ብቻም ሳይሆን በእኩልነት የተስተናገዱ ሆነው እንዲሰማቸው ማድረግ፣ በፍርድ አጻጻፍ ረገድ የቀረበው የፍርድ ሃተታ የሁለቱን ወገኖች ጥያቄ ያገናዘበ መሆኑን የሚያሳይ እና እንደፍ/ቤቱ ደረጃ በቂ ትንተና ያካተተ መሆኑ የሕዝብ አመኔታ ለማስገኘት ቁልፍ ነው፡፡ ይህ ሲሆን የፍ/ቤት ተገልጋዮች ውሳኔው እንኳን ልክ ባይመስላቸው ዳኛዋ በአድልዎ፣ በሙስና ወሰነችብኝ ሳይሆን ሕጉን በትክክል አልተረጎመችም በሚል ይረዱታል፡፡ ይህ ትልቅ ውጤት ነው፡፡

ፍ/ቤቶች የሚሰጧቸው ውሳኔዎች የነጻነት፣ የእኩልነት እና የእኩል እድል ጉዳዮች ላይ የተመሰረቱ በመሆኑ እነዚህ ጉዳዮች ሰፊ ግለሰባዊ ፣ ቡድናዊ / ሃገራዊ እንደምታ ሊኖራቸው ስለሚችል ለዳኞች ብቻ የሚተው ጉዳዮች አይደሉም፡፡ ሕጎች እንዴት ተተረጎሙ የሚለው ላይ ክርክሮች እና ትችቶች መካሄድ አለባቸው፤ ዳኞቹ ሕጉ፣ ፍሬ ነገሩን ተከትለው በሃላፊነት መንፈስ በምክንያታዊ ትንተና ላይ እስከተመረኮዙ እና በውሳኔአቸው ሙሉ እምነት እስካላቸው ድረስ በትችቶቹ ሊረበሹ አይገባም፡፡ አላማቸውም እውነተኛ የተከራካሪዎች አጫዋች እና ውሳኔ ሰጪ የመሆን እንጂ ማንንም ለማስደሰትም ሆነ ለማስከፋት አይደለም፡፡ በዚህ ከባድ ሃላፊነት ጥሩ ዳኛ ተብሎ ስም ማግኘት ግን ሕግን ማወቅ፣ ህግን መከተል፣ ሰፋ ያለ እውቀትን (ከሕግ ውጭ ያሉ ሁኔታዎችን ጭምር) መገንዘብ ከሚዲያ ተጽእኖ እና ከግል ስሜት መላቀቅን ይጠይቃል፡፡ የሚዲያ ተጽኖ በሶሻል ሚዲያ የመመስገን ፍላጎትን ያካትታል፡፡

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

የሕግ አተረጓጎም ጉዳይ የማያባራ የክርክር ጉዳይ ነው፡፡ መድረክ ሰጥተን በቅጡ ልንወያይበት ይገባናል፡፡ እንዲህ ያለው ውይይትም ጤነኛ ነው፡፡ በሌላ በኩል የፖለቲካ ፍላጎት ለማራመድ አፍራሽ እና አሳሳች መልዕክቶችን ከሙያዊ ትችቶች እና ክርክሮች የመለየት አቅም ሕዝቡ እያዳበረ መሄድ ይኖርበታል፡፡

## በእሴት ረገድ፡-

በእትራቴጂክ እቅድ ተዘርዝረው በአማካሪዎች ከሚቀርቡላችሁ እሴቶች ውስጥ በርካቶቹ ለፍ/ቤት በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ነጻነት፣ ወገኝተኛ አለመሆን፣ ጨዋነት ሁሉ ለፍ/ቤት ዋና የመመሪያ እሴቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሌላ "people-centered" "ሰው ተኮር" የሚለው ለግቤ ቅርብ ነው፡፡

ሰዎች ፍ/ቤት ሲመጡ መጉላላት፣ ግልጸኝነትን አለመተግበር፣ በቀጠሮ ማመላለስ የተፈጥሮ ግዴታ በሚመስል የስራ ባህል ውስጥ ነው ያለነው፡፡ እንደ ኖርዌይ ባለጉዳዮች ለፍ/ቤት ክርክር ከቤታቸው ሲንቀሳቀሱ በሆቴል ተቀምጠው በከፍተኛ እንክብካቤ ጉዳያቸውን አከናውነው እንዲመለሱ ለማድረግ ባንታደል በትህትና፣ መጉላላትን በመቀነስ፣ የተገልጋዮችን ስሜት በሚያረጋጋ፣ ከፍረሃት ነጻ በሆነ ሁኔታ አረፍ የሚሉበት መቀመጫ እንዲያገኙ ማድረግ ሮኬት ማምጠቅ ባይሆንም ገና በመለማመድ ላይ ነን፡፡ ነፍሰጡር ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን ቀድመው እንዲስተናገዱ ማድረግ ግዴታችን ነው፡፡ በዚህ ረገድ የጀመርናቸው የስልጠና እና የተጠያቂነት እርምጃዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡

የዳኝነት ስራ ከባድ ሃላፊነት ያለው ነው በሚል ይገለጻል፡ ይህ የሚባለው በሰዎች ሕይወት፣ ነጻነት፣ ንብረት ላይ ከከፍተኛ እስከመለስተኛ እንድምታ ስላለው ነው፡፡ በተለይ ሙያቸውን በሚያከብሩ ዳኞች ላይ የስራ ጫናውም ቀላል አይደለም፡፡ በአንጻሩ የማሻሻያ

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

እርምጃዎች እየተወሰዱ ቢሆንም የዳኞች የኑሮ ሁኔታም ከሃገራችን የኢኮኖሚ አውድ ውጭ ባለመሆኑ የተመቻቸ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ዳኞቻችን አቅዶ መስራትን፣ ጊዜን በአግባቡ የመጠቀም ክህሎት እጥረት ይፈታተናቸዋል፡፡ የመዝገብ ብዛትም ሌላው ጫና ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ፍ/ቤቱም ሆነ ዳኞች ነጻ ሆነው ይሰራሉ፡፡ ይህ ደግሞ ከሃላፊነት እና ተጠየቂነት ጋር የሚመጣ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ አንድ ተግባር ከላይ ወደታች በትዕዛዝ ሲሰራ ትዕዛዙን መተግበር ስለሆነ ቀላል ነው፡፡ በሌላ በኩል ነጻነት ከሃላፊነት ጋር ስለሚመጣ ማሰብ ፣ብስለት ማሳየት እና ሚዛናዊነትን ይጠይቃል፡፡ ይህ ጥቁር እና ነጭ ብቻ ሳይሆን በመካከል ያሉ በርካታ ቀለማትን መመልከት ትስስሮችንም መገንዘብን ይጠይቃል፡፡ በሁለንተናዊ መልኩ የዳኝነት ነጻነት ከተጠያቂነት ጋር የተጣመረ መሆኑ ሙሉ ግንዛቤ እየሰጠን ጥፋትም ሲኖር ተጠያቂ እያደረግን የምንሄድ ይሆናል፡፡

በንግግሬ ከዛሬው የስብሰባ አጀንዳችን ወጣ በማለት ከእቅድ ዝግጅት ሂደት በተጨማሪ ጠለቅ ብዬ መናገር የፈለኩት የትኩረት አቅጣጫችንን በመረዳት ከዚሁ አንጻር ግብዓት እንድትሰጡን በማሰብ ነው፡፡ በትዕግስት ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

## በመጨረሻም፡-

ስድስተኛውን አገር አቀፍ ምርጫ ለማከናወን የቀሩት ጥቂት ቀናት በመሆናቸው ለኢትዮጵያ መልካም እድል እመኛለሁ፡፡ ምርጫው በሰላም እንደሚከናወን ተስፋችን የላቀ ነው፡፡ ምርጫውን ተከትሎ የሚነሱ ክርክሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ በዚህ ረገድ አስፈላጊ ዝግጅቶችን ስላደረግን ፍ/ቤታችን ብቁ ውሳኔ ሰጪ ሆኖ እንደሚያገለግል ከወዲሁ አረጋግጣለሁ፡፡ መንግስት የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሕዝቡ ፍ/ቤቶቻችን ይህን ሃላፊነት መወጣት እንደሚችሉ ተገንዝባችሁ ከወዲሁ ተቋማዊ እምነት እንድታሳድሩ አደራ እላለሁ፡፡

የማትወዱት ውሳኔ እንኳን ቢወሰን ይግባኝ ማለት፣ ከዚያ ባለፈ ግን ውሳኔውን እንድታቀብሉ አደራ እላለሁ። ይህ የተቋም ግንባታ የጋራ ቃልኪዳን ነው።

**አመሰግናለሁ!**